የሰበር መዝገብ ቁጥር 22593

ቀን ሰኔ 6 ቀን 1998

ዳኞች 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

2. ዓብዱልቃድር መሐመድ

3. ጌታቸው ምህረቱ

4. መስፍን ዕቁበዮናስ

5. ወ/ት ሂሩት መለሰ

**አመልካች** ........ የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ

**መልስ ሰጭ** ... የአቶ ገ/ማርያም ዘለቀ ወራሾች

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍርድ

ይህ መዝገብ ለዚህ ችሎት ሊቀርብ የቻለው የሥር ፍ/ቤት የአሁኑ አመልካች ሲያስተዳድረው የቆየውን ቤት ለአሁኖቹ መልስ ሰጭዎች እንዲመልስና አለአግባብ የሰበሰበውን የቤት ኪራይ እንዲከፍል በማለት በተሰጠው ውሣኔ ቅር በመሰኘት ነው፡፡

የአሁኖቹ ተጠሪዎች በሥር ክሣቸው የአሁኑ አመልካች በወረዳ 20 ቀበሌ 44 ቁጥር 506 የሆነውን ቤት የተወረሰ ነው በማለት ይዞ እያከራየ የሚገኝ በመሆኑ ቤቱን እንዲያስረክባቸውና ከሰኔ 19 ቀን 1976 ጀምሮ ያለውን ኪራይ ብር 43.548 እንዲከፍል ጠይቀዋል፡፡ የሥር ፍርድ ቤትም የአሁኑ አመልካች ያቀረበውን የሥልጣን ጥያቄ ውድቅ በማድረግ የግራ ቀኙን ክርክር ሰምቶ ቤቱ ስለመወረሱ ማስረጃ አልቀረበም ብሎ በመደምደም ከፍ ሲል ቁጥሩ የተጠቀሰውን ቤት ለተጠሪዎች እንዲመለስ ፣ አለአግባብ

ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ቅጂው ከዋናው ጋር ተመሳሳይ
ፊርማ ---- ቀን 14/11/98

የሰበሰበውንም ገንዘብ ከነህጋዊ ወለዱ እንዲከፍል ውሣኔ ሰጥቷል። ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው ፍ/ቤትም ፍርዱን አጽንቶታል።

የአመልካች አቤቱታ ለሰበር ያስቀርባል ተብሎ ከተወሰነ በኋላ የግራ ቀኙ ክርክር 18/07/98 ተሰምቷል።

በዚህ ጉዳይ በዋንኛነት የተያዘው ጭብጥ ከአዋጅ ውጭ አለአግባብ የተወሰደ ንብረት ይመለስልኝ በሚል የሚቀርቡ አቤቱታዎችን አይቶ ለመወሰን ሥልጣን የተሰጠው ለየትኛው ክፍል ነው? የሚለው ነው።

እንደሚታወቀው ማንም ሰው በፍርድ ሊወሰን የሚገባውን (Just cable matters) ማናቸውም ጉዳይ በፍርድ ቤቶች ወይስ በህግ ሥልጣን ለተሰጠው አካል አስቀርቦ ማስወሰን የሚችል መሆኑን በመርህ ደረጃ በሕገ መንግሥቱ ቁጥር 37 (1) ላይ ተመልክቷል።

በዚህ መሠረት ሕገመንግሥቱ ወይም አግባብነት ያላቸው ሌሎች የማቋቋሚያ አዋጆች (enabling legislation) እንዲሁም የአገሪቱ የሥነሥርዓት ህጎችና ሌሎች ድንጋጌዎች የሚሰጡዋቸውን ሥልጣንና ተግባራት መሠረት አድርገው የዳኝነትና ሌሎች የአስፈጻሚው አካላት የሚቀርቡላቸውን አቤቱታዎች መርምረው የተለያዩ ውሣኔዎችን የሚሰጡ መሆኑም ይታወቃል። በዚህ ረገድ በአብነት ከሚጠቀሱት የውሣኔ ሰጪነት ክፍፍሎች መካከል በሕገ መንግሥቱ ቁጥር 62(1) እና 83 መሠረት የሚነሱ ሕገመንግሥታዊ ጥያቄዎችን አይቶ በብቸኝነት እንዲተረጎም ለኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት የተሰጠው ሥልጣንና ተግባር ለዳኝነትና ለሌሎች አካላት ውሣኔ ሰጪነት ሥልጣን ላይ ከተደረጉት የሥልጣን ክፍፍሎች መካከል አንዱና በዋነኛነት የሚጠቀሰው ክፍፍል ነው። በተመሣሣይ ሁኔታ ከፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥልጣን ውጭ ሕግ

ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ትክክለኛ ግልባጭ
ፊርማ ___ ቀን 14/11/98

# ውሣኔ

- የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ሐምሌ 22 ቀን 1996 በመ/ቁ.64108 የሰጠው ውሣኔ እና በፌ/ከ/ፍ/ቤት ታህሣሥ 20 ቀን 1998 በመ/ቁ.3408 የሰጠው ትዕዛዝ ተሽሯል፡፡
- የአሁኖቹ ተጠሪዎች ከአዋጅ ውጭ ተወሰደብን የሚሉት ንብረት ካለ በህግ አግባብ ሥልጣን ለሚኖረው ክፍል አመልክተው ከሚያስወስኑ በስተቀር በሥር ፍ/ቤቶች ውሣኔ ተጠቃሚዎች ሊሆኑ አይችሉም፡፡
- የዚህን ፍ/ቤት ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡
- መዝገቡ ያለቀለት ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ወ/ፊ

ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ትክክለኛ ግልባጭ
ፊርማ [signature] ቀን 14/11/98

አውጭው አስፈጻሚ አካላቱና በሥራቸው የሚገኙ ክፍሎች በተለይ እንዲያከናውኑአቸው የሚያስፈልጉ ጉዳዮችን አይተው ተገቢዎቹን ውሣኔዎች በብቸኝነት እንዲሰጡ የሥልጣን ድልድል የሚያደርጉባቸው አሠራሮችም ያሉ መሆኑን እነዚህን አካላት ለማቋቋምና ሥልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን የወጡትን የማቋቋሚያ አዋጆች ብቻ መመልከቱ በቂ ሊሆን ይችላል፡፡ በዚህ ረገድ በአዋጅ ቁጥር 345/95 አንቀጽ 48(1)፣ 49 እና 50 መሠረት ከማኀበራዊ ዋስትና ጥያቄዎች ጋር የሚነሱ የጡረታ መብት ክርክሮችን አይቶ እንዲወስን ለባለሥልጣኑ መ/ቤት የተሰጠ ብቸኛ የውሣኔ ሰጭነት ሚና እንዲሁም በአዋጅ ቁጥር 110/87 መሠረት ከአዋጅ ውጭ የተወሰዱ ንብረቶች ላይ የሚቀርቡ አቤቱታዎችን እንዲወስን ለኢትዮጵያ ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ የተሰጡ ሥልጣንና ተግባራትን ማየቱ በዚህ ረገድ ለመግለጽ የተሞከረውን እውነታ በግልጽ የሚያመላክቱ ናቸው፡፡ በአጠቃላይ የሕገመንግሥቱና የሌሎች ሕጎች ድንጋጌዎች በመመርመር ሊደርስበት የሚችለው ድምዳሜ ቢኖር ፣ የኢትዮትያ የዳኝነት አካላት የሥልጣን ምንጫቸው ከሆነው ሕግ ውጭ ማናቸውንም ጉዳዮች ተቀብለው ለመወሰን የሚያስችል ተፈጥሯዊ አወቃቀር (inherent power) የሌላቸው መሆኑን ልብ ሊሉ ይገባል፡፡

ወደያዝነው ጉዳይ ስንመለስ የአሁኖቹ ተጠሪዎች በሥር ክሳቸው የአሁኑ አመልካች ቤታቸው ሳይወረስ ከአዋጅ ውጭ ወስዶ እያከራየ መሆኑን ገልፀው በህገወጥ መንገድ የወሰደውን ቤት እንዲመለስላቸው እያከራየ የሰበሰበው ገንዘብ እንዲከፍላቸው ላቀረቡት ክስ የአሁኑ አመልካች የፍ/ቤቱን የሥልጣን ችሎታ መሠረት አድርጎ ተቃውሞ አቅርቦ የነበረ ቢሆንም ጉዳዩ የቀረበለት ፍ/ቤት በሥልጣን ጥያቄው ላይ ከአዋጅ ቁጥር 110/87 መንፈስ ውጭ የተሳሳተ ትርጉም በመስጠት ጉዳዩን ተቀብሎ ውሣኔ መስጠቱ መሠረታዊ ስህተት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ትክክል ግልባጭ
ፊርማ [signature] ቀን 14/11/98